1›ከሰማያት ወረደ

ከሰማያት ወረደ ወእም ማርያም ተወለደ
ከመይኩን ቤዛ(2) ለኩሉ አለም
ወለብሰ ስጋ ማርያም
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወልደ
እንዲሆነን ቤዛ(2) ለዓለሙ ሁሉ ለበሰ የማርያምስጋ

2.ይኸው ተወለደ

ይኸው ተወለደ የአለም መድሃኒት (2)
እሰይ ተወለደ የአለም መድሃኒት (2)
አዝ ›››››››››››››››
ትንቢት ተናገሩ ነብያት በሙሉ {3)
አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ (2)
አዝ ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ሰብዓ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ (3)
የእስራኤል ንጉስ ተወልዲል እያሉ(3
አዝ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ሰብዓሰገል መጡ ያዘው እጅመንሻ (3)
ወርቅእጣን ከርቤውን ለማርያም
እጅመንሻ(3)
አዝ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ሀፃናት እንሂድ ከልደቱ ቤት (3)
ውሃ ሆንዋልና ማርና ወተት (3)
አዝ ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
በሶርያ ታየ ፈጣሪ እንደእንግዳ (3)
ብስራተ ልደቱን ለሁሉ ሊያስረዳ (3)

3.በበረት ተኛ

በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ
የአለም መድሃኒት (2) ዛሬ ተወለደ

4. በበረት የተኛው

በበረት የተኛው ቅዱሱ ሀፃን
ለአለሙ ሁሉ ሆነልት ምድሀን
ምስክር ሊሆኑት ለፍፁም መንግስቱ
ትንፋሽ ገበሩለት ከበው እንስሳቱ
እሰይ የምስራች ሀሌ ሀሌ ሉያ
ጌታ ተወለደ ከድንግል ማርያም

5.እንፈራው /ረኪቦሙ

አንፈራው ሰብዓ ሰገል ረኪቦሙ ሀፃን ሀፃን
ዘተ ወልደ ለነ (4) ሀፃን ዘተወልደ ለነ

6.እንፈራው ሰብዓ ሰገል

አንፈራው ሰብዓ ሰገል(2)
አምሃ ኦሙ አምፅዑ መድምመ

7.አይኖቼ ማዳኑን

አይኖቼ ማዳኑን አይተዋልና (2)
ይገባዋል(2) ክብርና ምስጋና
አዝ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ከሰማያት ወርዶ ሰውን በማፍቀር
ሀያሉ ጌታችን ቸሩ እግዚዓብሄር
በቤቴሌም ዋሻ በዚያ በግርግም
ተወለደ ዛሬ መድሐንያለም
አዝ ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹

የተነበዩለት ብዙ ነብያት

ከድንግል ተወልዶ አዳነን በእውነት
ከበደል ጉራንጉር አወጣን ከትቢታ
በአንድነት እንዘምር እንበል ሀሌ ሉያ
አዝ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹

የተናቅን ስንሆን እኛን ሊያድን ወርዶ
በፍቅር አከበልን እራሱን አዋርዶ
ምን አያነት ፍቅርነው ፍፁም ምህረት
የአምላክ መወልድ በክብቶች በረት

8.አንቺ አንቺ ቤቴልሄም

አንቺ (2) ቤቴልሄም የይሁዳ መሬት
ካንቺ ተወልደ የአለም መድሃኒት

አዝ አዳም ክብር ሲሻ ቤቴልሄም
ለሁሉ ስላም
ጌታ ተውለደ
ከድንግል ማርያም
አዝ እጅ ምንሻ አቀረቡ ቤቴልሄም
የምስራቅ ነገስታት
በክብቶቹ በረት
ተኝቶ ላገኙት
አዝ እስራኤል ህዝቤን ቤቴልሄም
የሚጠብቃቸው
ካንቺ ይወጣል ብሎ
እንደነገራቸው
አዝ ቅዱሳን ህዝቤን ቤቴልሄም
ያምስገኑት
ስብሀት ለእግዚአብሄር
ብለው ዘመሩልት
አዝ አንቺ ቤቴልሄም ቤቴልሄም
እንዴት ታድለሻል
ኢዮርና ራማ
ኤረርን መስለሻል

9.በነል ሰከበ

በነል ሰከበ በአዕርቅት ተጠብለለ
ብዛ ኩሉ አለም ዩም ተወልደ

10.ዮም ሰማያዊ

ዩም ሰማያዊ በነል ሰከበ ለዘ ተወልደ እም ቅድስት
ርእም ኖሎት (2)አእኮትዎ መላዕክት (2)

11. ለዘ ተወልደ

ለዘ ተወልደ እም ቅድስት ድንግል
ምንተንብሎ ናስተማስሎ ለመዳኒነ
አርዊ ገዳመኑ አንብሳ
ወሚኢመ(2)ከራድዮነ

12 .በነ ለእንስሳ

በነ ለእንስሳ (2)
በነ ለእንስሳ ተወልደ አማኑኤል (2)

13 .በቤቴልሄ ተወልደ

በቤቴልሄም ተወልደ (2)አማኑኤል
እም ዘራ ዳዊት (2) ተወልደ
አማኑኤል

14 .ወወልደት

ወወልደት ወልዳ ዘክብራ (2)
መንጠላይት ደመና ሠወራ ‹2)

15.ተወልደ ኢየሡሰ

ተወልደ ኢየሱስ በቤትልሄም (2)
ዘይሁዳ በቤቴልሄም
አዋል ደ ጢሮስ አምሃ ይሰግዳ (2)
በቤቴልሄም

16.ሣርቅጠሉ ሰርዶ

ሣርቅጠሉ ሰርዶ ሰንበሌጥ ቁጢማው
በዛች ቀን በዚያች ዕለት ለምለለም መነበረ
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው
ጌታ መወለዱን አምስራች ሰምተው
እልል ቤዩ ቤቴልሄም ሃሌ ሃሌ ሉያ
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ 2)
አዝ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ያ ትንቢ እረኛ ሳለ በትጋት
ብርሃን ለብሶ ተየ በእኩለ ለሊት
ጥሪ ተልኮለት ከሰማይ ሰራዊት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
አዝ
የእረኝነት ስራ ተንቆ እንዲቀር
ብሎ ሰው በልማድ ደነግጎ ነበር
አምላክ የመረጠው መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ
አዝ
የተነበዩለት ነብያት በሙሉ
ጌታ ተወለዳ የምስራች በሉ
ሰውን በመውደዱ ሰማያዊው ንጉስ
ይኸው ተወለደ እኛን ለመቀደስ
አዝ
የሩቅ ምስራቅ ሰዎች ሰባ ሰሀል
ሰምተው
ሊሰግዱለት መጡ በኮከብ ተመርተው
እጣንና ከርቤ ወርቁንም አመጡ
እንደየ ስርዓቱ እጅ መንሻ ሰጡ
አዝ
ስለ ተወለደ መድን የኛ ተስፋ (2)
በድል ተወገደ ሀጥያትም ጠፋ (2)

17. ***በወንጌል አናፍርም***

በወንጌል አናፍርም አማኑኤል
ተወልደ አማኑኤል
ለኛ መመኪያችን " " "
እንመሰክራለን " " "
ነው መዳኒታችን " " "
የጠፋውን ሊያድን " " "
ወረደ ከላይ " " "
የበጎች እረኛ " " "
'አምላክ አዶናይ " " "
እም ድንግል (4) ተወልደ አማኑኤል
አዝ ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
የነገስታት ጌታ አማኑኤል ተወልደ
ቤዛ ኩሉ አለም
መድህን ተወለደ
በቤቴልሄም
አንቺ ቤቴልሄም
ምንኛ ታደልሽ
የአለም መድሃንት
ተወለደብሽ
አዝ ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ከልዑል መንበሩ አማኑኤል ተወልደ
ከዙፋኑ ወርዶ
ትዕትታን ሰበክ
በበረት ተወልዶ
የአለም ሁሉ አምላክ
የማመመሻር ቃሉ
ተሰበክ ዛሬ
ለአለሙ ሁሉ
አዝ ‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹‹
ተራሮች ዘለሉ አማኑኤል ተወልደ
አማኑኤል
ሊያመሰግኑት
ዕፀዋት ሳይቀሩ
የዱር አራዊት
ቀላያትም ሁሉ
ማርና ወተት
ዕፁብ ነው ድነቅ ነው
የጌታ ልደቱ

18.ከመቤታችን ተወልዶ

ከመቤታችን ተወልዶ ስጋን
የለበሰው(2)
እኛን ሊያድነን ነው(2)ከሞት እኛን
ሊያድነን ነው
በቀራንዮ ተሰቅሎ ሞትን ድል
ያደረገው (2)
እኛን ሊያድነን ነው (2)ከሞት እኛን
ሊያድነን ነው
በሦስተኛው ቀን ተነስቶ ሞትን ድል
ያደረገው
እኛን ሊያድነን ነው(2) ከሞት እኛን
ሊያድነን ነው

19.በኮከብ መቁ

በኮከብ መውኡ (2) ሰብዓ ሰገል (2)
ለአማኒኤል ይስግዱ ሰብዓ ሰገል

20.ውስጠ ማህፀን

ውስጠ ማህፀን ድንግል ኀደረ
ማህፀነ ድንግል (2)
ሰማይ ወምድር ዘኢ.ያገምሮ (2)
በማይ ተጠምቀ

21.ክርስቶስ ተወልደ

ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀ በማይ
ወለደነ ዳግመ እማይ (2)
ዳግመ(2) ወለደነ ዳግመ እማይ

22 . አምላክ ሰው ሆነ

አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ
በድንግል ማርያም ተከናውነ
አዝ የአብ ሙሽራ የወልድ እናቱ
የመንፈስ ቅዱስ ፅርረ ቤቱ
በሰማይ ሆኖ አብ የፀናሽ
ወልድ ለራሱ ቤቱ አረገሽ
መንፈስ ቅዱስ ነው(2) የፀለለሽ
አዝ ከሦስቱ አካል ወንድ አንድ አካል
መጣ ወረደ በኀባው ቃል
ተፀንሶ ሳለ ወልድመ ከእናቱ
አልተነጠለም ከ ሦስትነቱ
ታምራት አርኃል ድዌ
ፈውሶል በአምላክነቱ
አዝ ይህን ድንቅ ሚስጢር በሉ ግሩም
ምስጋና አቅርቡ ለዘለዓለም
በስነ ፍጥረት ይታወቃል
የአለም ፈጣሪ የእግዚአብሄር ቃል
ደስ ይበላችሁ ደስ ይበለን በሉ
እልል

23 .በፍቅር ተሰቦ

በፍቅር ተሰቦ ወረደ ለኛ ሲል
የፍቅሩን ፍፃሜ ገለፀው በመስቀል
ለእኛ ያላረገው ከቶ ምን አለና
አፋችን ዝም አይበል እናቅርብ
ምስጋና
አዝ ደስ ይበለን ከሰማያት ወርዶ
ተላቁ አባታችን
የዘመናት ንጉስ
ኢየሱስ ጌታች
ከኤፍራታ ወጣ
ከዳዊት ከተማ
ተወልዶ ማደሩን
ምስራች ተሰማ
አዝ እንዳንተ ያለ በሀየያዋ ውስጥ
ወድቀን
ስንኖር ተጎሳቅለን
አምላክ የኔ ጌታ
ከሞት ውስጥ አዳንከን
ዝናውንም አውሩ
ለአህዛብ ሁል
እንዳ እግዛብሄር ያለ
ማንም የለም ብሉ
ደስ ይበለን ወረደ ወደ ምድር
ሰላሙን ሊሰጠን
ሰላም ለናንተ ይሁን
ብሎ ሊሰብክልን
በመስቀል ተሰክሎ
እኛን የተቤዠ ን
ከሲኦል እስራት
በፍቅሩ የፈታን
አዝ ሀሎ ሉያ ምስጋና በስማይ
ምስጋን በምድር
ሁሉን ቻይ ለሆነው
ለቸሩ እግዚአብሄር
ሆሎ ሉያ ለርሱ
ለነፍሳችን ጌታ
ዝማሬን እናቅርብ
ከጠዋት እስከ ማታ

24. እም አምላክ ሙሽራ ነሽ

እምአምላክ ሙሽራ ነሽ(2)
ለቃል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ እኸ
(2)
አዝ
አስራ ሁለት አመት ቤተመቅደስ
የኖርሽ
የመመረጥ ፀጋ ከአምላክሽ ያገኘሽ
አምላካዊ መላዕክ ዕውብ ድንቅ ዜና
ከሰማያ መጣልሽ አቂርጦ ደመና
አዝ
በስድስተኛው ወር ገብርኤል ተልኮ
ቤተ መቅደስ መጣ ሊያበስርት
ለድንግል
በልዩ ሰላምታ ሰላም ለኪ ያለሽ
የክርስቶስ እናት በጣም ደስ ይበልሽ
አዝ
መላዕክት በሰማይ ያመሰግኑሻል
ክብር ለአምላክ እናት ይድረስሽ
ይሉሻል
በማህጸንሽ ሊያድር የሰራዊት ጌታ
ለመሆን ተመረጥሽ ያምልክ ቅዱስ
ቦታ
አዝ
የፈጣሪ እናት መሆንሽን ተረድቶ
ሰላም ላንቺ ይሁን አለሽ እጅ ነስቶ
ከፍጡራን ሁሉ አንቺ ስለከበርሽ
ገብርኤል ተልኮ ደስታን አበሰረሽ
አዝ
ምንኛ ድነቅ ነው ድንግል ያንቺ
ብስራት
ጌታን ትወልጂያለሽ የሚል ቃልን
መስማት
ይሁንልኝ ብላ ቃሊን ተቀበለች
ድንግል ሆይ እናቴ እጅግ ልዩ እኮ
ነሽ
አዝ
ንፅህት ሙሽራ ጌታ ያደረብሽ
ድንግል ለኛም ይድረስ ፀጋ በረከትሽ
ማንም አልተሰጠው ከፍጡር እንደሰዋ
እኛንም ይጎብኘን ቅዱሱ መንፈሳዋ

25.ማርያም (3) ደስ ይበልሽ

ማርያም(3)ደስ ይበልሽ በገብርኤል
ሰላምታ
ባንቺ ስላደረ ያለም ሁሉ ጌታ (2)
አዝ
ያምላክ ቸርነቱ ፍቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጠ ብርሀን
መድሀኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ
አዝ
ድንግል ተቀምጣ በቤተ መቅደስ
ሀርና ወርቁን ስትፈትል ንግስት
ገብርኤል (2) ዜንዊ ሀዲስ
የአምላክን መወለድ ስጋን በመልበስ
አዝ
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ለትሰማ
በሱዋ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ
እውነተኛ መላክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

26. እመቤቴ ጥላ ከለላዮ

እመብቴ ጥላ ከለላዪ እረዳቴ የገነት
ሙሽራ (2)
የገነት ሙሽራ(3) ማርያም የልዑል
ማደርያ
አዝ
መጣ ከነብያት ቃልዓብ ተሰብኮ
በስድስተኛው ወር ገብርኤል ተልኮ
ቤተ መቅደስ ሳለቸ በፍፁም ትህትና
ደስ ይበልሽ አላት መላኩ መጣና
በጥሁም ቃል እርሳን እያፅናና (2)
አዝ
እኔ ወንድ ሳላውቅ ይሄ እንዳት
ይሆናል
ብላ ጠየቀችው በትህትና ቃል
ገብርኤልም አላት አትፍሪ ማርያም
እግዚአብሄር ፍፁም ነው የሚሣነው
የለም (2)
አዝ
መንፈስ ቅዱስ ቀርቦ ይፀልልሻል
የልዑሉም ሀይሉ ባንቺ ያድርብሻል
ካንቺ ሚወለደው ቅዱስ የእግዚዓብሄር
ልጅ
ይሆናል ዘላለም ዓለምን የሚዋጅ (2)
አዝ
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች
በፍጹም ተዋህዶ ያምላክ እናት ሆነች
ድንግል ማርያም በእውነት ልዩ ነች
(2›

27.የምስራች

የምስራች ደስ ይበለን (2)
የአለም መድሀኒት ተወለደልን (2)
የምስራች ተወለደልን(2)
አዝ
ንጉስ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ (2)
ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ(2
አዝ
ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት (2)
በኮከብ ተመርተው ኮከቡን አገኙት(2)
አዝ
ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው (2)
ወርቅና እጣኑን ከርቤውን ሰጥተው (2)

28.ስብሃት ለእግዚዓብሄር

ስብሃት ለእግዚአብሄር ወሰማያት (2)
ወሰላም ወምድር ስምረቱ ለሰብ
ሀሌሉያ (3)አሜን ሀሌሉያ

29.ይኸው ተወለደ

ይኸው ተወለደ <u>የአለም መድሀኒት</u> (3)
እሰይ ተወለደ <u>የአለም መድሀኒት</u> (3)
አዝ
ትንቢት ተናገሩ <u>ነብያት በሙሉ</u> (3)
አምላክ ቀዳማዊ <u>ይወርዳል እያሉ</u>(3)
አዝ
ሰብዓ ሰገል መጡ <u>ሊሰግዱ በሙሉ</u>(3)
የእስራኤል ንጉስ ተወልድዋልእያሉ(3)
አዝ
ሰብዓ ሰገል መጡ <u>ይዘው እጅመንሻ</u>(3)
ወርቅ እጣን ከርቤ <u>ለማርያም እጅ መንሻ</u>(3)
አዝ
ህፃናት እንሂድ <u>ከልደቱ ቤት</u> (3)
ውሃ ሆንዋልና <u>ማርና ወተት</u>(3)

30.በፍስሃ /2/ወበሰላም

በፍስሀ /2/ ወበሰላም /2/
ወረደ ወለወድ /4/ወልድ ውስተ ምጥማቃት /2/
ትርጉም ወልድ ክርስቶስ ከሰማያት ወደ ወንዞች ወረደ

31.ሆረ እየሱስ

ሆረ እየሱስ /2/
እም ገሊላ /3/ ሀበ ዮሀንስ /2/
ትርጉም ፡ ሄደ እየሱስ /2/
ከገሊላ /3/ ወደ ዮሀንስ /4/

32. እግዚኦ መርሃ

እግዚኡ መርሀ ዮርዳኖስ አብፅሀ/2/
ወበህየ ዮሀንስ ወበህየ ፍፁመ ተፈስሀ /2/
ጌታውን መራና ዮርዳኖስን አደረሰው /2/
በዚህም ዮሀንስ በፍፁም ደስ አለው /2/

33.ይትፈስሁ

ይትፈስሁ ሀድባረ ፂዮን
ወይታስያ አዋልደ ኢትዮጵያ/2/
እስመ ተወልደ ብሁተ ልደት
መድሀንያለም በኢየሩስ አሌም
መድሀንያለም

34. ተወለደ እኸ

ተወለደ እኸ የአለም መድኅን
የአለም መድኅን (4) ተወለደ

35.ወረደ ወልድ

ወረደ ወልድ /3/
እም ሰማያት ውስተ ምጥማቃት/2/

36.እንደ ዮሴፍ

እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሶሎሜ በሆን በሆን
እየሩስአሌም/3/ አምላክ ሲወለድ ባየን /2/

37.እም ሰማያት ወረደ

እም ሰማያት ወረደ ወድንግል ማርያም ተወለደ/2/
ከመ ይመኩን ቤዛ ለኩሉ አለም
ወለብሰ ስጋ ማርያም/2/
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ/2/
እንዲሆነን ቤዛ ለመላው አለም ለበሰ
የማርያምን ስጋ/2/

38 .እናትህን

እናትህን እኸ አባትህን አክብር /2/
አትስረቅ አትግደል አታመንዝርም /2/

39.ሃሌ ሉያ

ሃሌ(3) ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ
ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መፈታዊ(2)
ሃሌ(3) ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ ጥምቀትህ

<u>40.በ30 ክረምተ</u>

በ30 ክረምተ በዬርዳኖስ ተጠምቀ /2/
በዬርዳኖስ //2/ዬርዳኖስ /2/
ተጠምቀ በዬሐንስ/2/

<u>41.ቀዳሚሁ ቃል</u>

ቀዳሚሁ ቃል ውዕቱ ቃል /2/
ቃል ሥጋ ኮነ ይቤ ዬሐንስ /4/

<u>42. እሳተ ፅሩፅ</u>

እሳተ ፅሩፅ ማየ ጠፈሩ /2/
ደመና መንኩራኩሩ ለመድኃኔዓለም /4/

<u>43.ተጠመቀ</u>

ተጠመቀ እኸ የዓለም መድኅን /2/
የዓለም መድኅን /4/ ተጠመቀ

<u>44.ወረደ ወልድ</u>

ወረደ ወልድ /6/
እምሰማያት ውስጠ ምጥምቃት /2/
ትርጉም፡ ወልድ ክርስቶስ ከሰማይ ወረዶ
/ወዶ/ ወንዞች ወረደ

<u>45.ነድ ለማየ ባህር</u>

ነድ ለማየ ባህር ከበቦ /2/
ማየ ባህር ኀበ የሐውር ፀበቦ /4/
ትርጉም፡ የባህር ውሀ እሳት ከበበው
የባህር ውሀም የሚሄድበት ጠበበው

<u>46. አማን በአማን</u>

አማን በአማን /2/
መንክር ስብሐተ ጥምቀቱ /2/

<u>47. ኢየሱስ ሖረ</u>

ኢየሱስ ሖረ ሀገረ እሴይ /2/
ዮሐንስ አጥምቆ በማይ /4/
ትርጉም፡ ኢየሱስ ወደ እሴይ ምድር ሔደ
ዮሐንስ በውሀ አጠመቀው

<u>48. ጥምቀት አንዲት ናት</u>

ጥምቀት አንዲት ናት /3/
እኸ ክርስቶስ ነው ጥንት የመሰረታት /2/

<u>49.ዮሐንስኒ ሀሎ</u>

ዩ ሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ /2/
በሄኖን በቅሩበ ሳሌም /2/
ትርጉም፡ ዮሐንስ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያጠምቅ ነበር

<u>50. ጎዲጎ ተሰፃ</u>

ጎዲጎ ተስፃ ወተስዓተ ነገድ ነገድ /2/
ማዕከለ ባህር /4/ ቆመ ማዕከለ ባህር /2/
ትርጉም፡ ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላዕክት ትቶ በባህር መካከል ቆመ

<u>51. እኸ ጎዲጎ ተሰፃ</u>

እኸ ጎዲጎ ተስፃ እኸ ወተስዓተ ነገድ /2/
እኸ ማዕከለ ባህር ቆመ ማዕከለ ባህር /2/

<u>52. ዮሐንስ አጥምቆ</u>

ዮሐንስ አጥምቆ ለኢየሱስ /2/
በፈለገ ዮርዳኖስ በፈለገ ፈለገ ዮርዳኖስ /2/

ትርጉም፡ ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው

<u>53. መፅአ ቃል</u>

መፅአ ቃል እምደመና ዘይብል /2/
ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቀረ /2/
መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል /2/
የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው /2/

<u>54. እንዘ ሕፃን</u>

እንዘ ሕፃን ልህቅ በዮርዳኖስ ተጠምቀ /2/
በዮርዳኖስ /2/ ተጠምቀ በዮሐንስ /2/
ትርጉም፡ ሕጻን ሆኖ ጥቂት በጥቂቱ አደገ
በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

<u>55.በዕደ ዮሐንስ</u>

በዕደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ
ሰማያዊ /5/ ኢየሱስ ናዝራዊ
ትርጉም፡ ሰማያዊው የናዝራቱ ኢየሱስ በናዝራቱ በኢየሱስ እጅ ተጠመቀ

<u>56.አምላክ ከዮርዳኖስ</u>

አምላክ ከዮርዳኖስ /2/ ተጠምቆ ሲወጣ /2/
ሰማያት ተከፍተው /3/ ከሰማይ ቃል መጣ /2/
ቃሉም እንዲህ ነበር /2/
እንደሚከተለው /2/
የምወደው ልጄ /3/ ይሄ ነው የሚለው /2/
ዘጠና ዘጠኙን /2/ መልእክትን ትቶ /2/
አምላክ ተጠመቀ /3/ ከዮርዳኖ ስ ገብቶ /2/
ዕፁብ ነው ድንቅ ነው /2/ ይገርማል በውኑ /2/
ሰማያዊው አምላክ /3/ ምድራዊ መሆኑ /2/
አብ የነገረለት /2/ በደመና ወርዶ /2/
ተጠምቆ አዳነን /3/ ከድንግል ተወልዶ /2/

<u>57, በመንፈስ ይሐውር</u>

በመንፈስ ይሐውር እምኃይል ውስተ ኃይል
ካህን /2/ ወነቢይ ካህን ወነቢይ
ዮሐንስ መጥምቅ
ትርጉም፡ ከኃይል ወደኃይል በመንፈስ ይሄዳል
ዮሐንስ መጥምቅ ካህንና ነቢይ ነው

<u>58.ንሴብሆ</u>

ንሴብሆ /2/ ለእግዚአብሔር /2/
ስቡሃ ዘተሰብሃ /2/
አዝ.....
ባህሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ
በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ
ከባርነት ቀንበር ፍፁም ነፃ ወጣን
ህይወት የሚሆነን መና ነው ምግባችን
አዝ.....
እናመስግነው /2/ እግዚአብሔር /2/
ምስጉን ነው የተመሰገነ /2/
አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር

ጉልበታችን ቢዝል ፈተና ቢበዛ
ኃይላችን ጌታ ነው የዓለም ሁሉ ቤዛ
አዝ……..
ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆልን ጠጣን
ይህን ኃያል ጌታ ኑ እናመስግን
ህዝቦች ደስ ይበለን ህይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

59. ዮሐንስኒ

ዮሐንስኒ ያጠምቅ /2/
በሂኖን /4/ በማዕዶተ ዮርዳኖስ /2/
አዝ……..
ዮሐንስ ሲያስተምር ያጠምቅ
በጫካ በሜዳ " "
ግመል ፀጉር ለብሶ " "
ሆኖ ምድረበዳ " "
አዝ……..
ጌታውን የሚወድ " "
ብዙ ሰው እያለ " "
ጌታውን ለማጥመቅ " "
ዮሐንስ ታደለ " '
አዝ ……..
ተራራው ዝቅ ይበል " "
ጠማማውም ይቅና " "
ብሎ ያስተማረው " "
ዮሐንስ ነውና "
አዝ ……
ከኃጢያት ተለዩ " "
በውኃ ተጠመቁ " "
መንግስተ ሰማያት " "
እንዳለች እወቁ " "

60.ጥምቀተ ባህር

ጥምቀተ ባህር ዮርዳኖስ ነያ /2/
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ /2/
አዝ……..
ጌታችን ሲጠመቅ ባህር ምን አለች
አልችለውም ብላ ወደኋላ ሸሸች
ብርሀነ መለኮት በወንዙ ሲመላ
ዮርዳኖስም ሸሸ ሔደ ወደኋላ
አዝ…….
አብ በመጣ ጊዜ ደመናውን ጭኖ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በእርግብ አምሳል
ሆኖ
ለልጅ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና
ቃሉን ተናገረ ሆኖ በደመና
አዝ……..
ጌታችን ሲጠመቅ በሰላሳ ዓመት
ባህር ኮበለች ግዑዟ ፍጥረት
ሰማይ ተከፈተ ሆነልን ፀዐዳ
ምስጢረ ስላሴ ታወቀ ተረዳ
አዝ……..
እልል በይ ዮርዳኖስ የጥምቀት መገኛ
የፅድቅ መሰላል ድኅነታችን ለእኛ
ቀላያት አብርህት ብዙዎች እያሉ
እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

61.የዓለምን በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ /2/
አዝ……
የሰማዮች ሰማይ የማይችሉት ንጉስ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደፈረስ
አዝ……
ባህር ስትጨነቅ ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ
አዝ……
ልጅ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየመሰከር የልጁን ጌትነት
አዝ……
እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በእርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ
አዝ……
ባህር ስትጨነቅ ተራራው ሲዘምር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
አለም በዛሬ ቀን አየች ታላቅ ምስጢር

62.ፈለገ ዮርዳኖስ

ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕም
የ ክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ
መቅድም
አዲሱ ሙሽገራ ሲመጣ ያያችሁ
የዮርዳኖስ ምንጮች ስለምን ሸሻችሁ
/2/
አዝ……
እናንተ ተራሮች እግር ሳይኖራችሁ
እንዴት እንደ ጊደረ ሸቅብ ዘለላችሁ
የግመል ደበሎ ለብሶ ስላያችሁ
መዋምቁ ዮሐንስ አውሬ መሰላችሁ
/2/
አዝ……..
የአንበሳ ድምጽ ነው ወይስ የደስታ
መቼ ተማራችሁ እንዲ ያለ
ግርግርታ
ቅዱሱ ዮርዳኖስ አይ የጌታ ሀገሩ
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአንተ
ላይ ሰፈሩ /2/
አዝ…….
ጌታዬ ያላንተ የለምና ሕይወት
ተጠምቀን ስንዘምር ስጠን ዳግም
ልደት
ያለ ተፈጥሯቸው ወንዞች እልል አሉ
ሊዘምር ይገባል የሰው ልጅ በሙሉ

63. ኦ ክርስቶስ

ኦ ክርስቶስ ኦ አምላክ ብሩህ ነህ /2/
ልቦናዬን አብራው በጥዑ ም ቃልህ /2/
አዝ…….
የናሆም ደመና ክርስቶስ
ልቤን አለምላሜ ››
እነሙሴን በሆንኩ ››
እንዳይህ ቀድሜ ››
የዮርዳኖስ ውሀ ››
በላዬ ሲፈላ ››
ዮሐንስን በሆንኩ እንዳይህ በተድላ
አዝ……..
ነበልማል ሐመልማ ክርስቶስ
ተዋሕዶ ሲና ››
ልቤ ከሩቅ ሆኖ ››
ተመልክቷልና ››
በቀረበ ጊዜ ››
ነገሩን ሊረዳ ››
ለእስራኤል ሾምከው ሕዝቡን
እንዲመራ
አዝ……..
ሙሴ በበትሩ ክርስቶስ
ኤርትራን ሲመታ ››
ተሻገሩ እስራኤል ››
በንፁ በደስታ ››
ያልተደሰቱማ ››
የፈርዖን ሰራዊት ››
እየተሰጠሙ ቀሩ ወደኋሊት
አዝ…….
ትንቢቱ ፀደቀ ክርስቶስ
የኢሳያስ ››
ድንግል ወለደች ››
በመንፈስ ቅዱስ ››
ምነው ባደረገች ››
እንደነሰሎሜ ››
ጌታዬ ሲወለድ ለማመስገን ቆሜ
አዝ…….
ሐዋርያት ሁሉ ክርስቶስ
ዞረው ያስተማሩ ››
ወንጌል ብርሀን ነው ››
የዓለም መድኃኒት ››
ዮሐንስ እንዳለው ››
ጥምቀት ለንስሀ ››
እጠመቀዋለሁ የኃጉህን ውሀ
አዝ…….
ሚካኤል በቀኝህ ክርስቶስ
ገብርኤል በግራህ ››
ቅውማን የሆኑ ››
ሁሉም በእየተራ ››
ሡራፌል ኪሩቤል ››
ኃይላቸው የበዛ ››
ያመሰግኑሀል አንተን የዓለም ቤዛ

64. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሠሬር /2/
እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም
/4/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ
/2/
የዓለም ቤዛ ነውና የማኅፀንሽ ፍሬ /4/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ
ተወልዶ /2/
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን
ለመቀደስ /4/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ዕዳችንን ፋቀ
/2/
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን /4/
በድንግልና የወለድሽው የአንቺ ፅንስ
/2/
የድኩማኖች ብርታት ነው የሕሙማን
ፈውስ /4/
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም የዘከረ /2/
በመንግስተ ሰማይ ይኖራል
እንደተከበረ /4/
ብርሀነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ /2/
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል
አንቺ ነሽ /2/
እመቤታችን እናታችን ማርያም /2/
የተማፀነሽ ይኖራል ለዘልዓለም/4/

65. መጥምቀ ለመኮት

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ /2/
መንገድ ጠረገ ለኢየሱስ መምጫው
ሲደርስ /2/
ተክለ ሀይማኖት በፀሎት /3/ የእኛ
አባት
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያ /2/

ኢቲሳ መጥተው ፀለዩላት ለኢትዮጲያ
/2/
ዜና ማርቆስ በፅኑ እምነት /2/
ፀሐይ አቆሙ እንደ ኢያሱ በደብረ
ብስራት /2/
እመቤታችን ድንግል ማርያም /2/
ምህረት አሰጪን ከመለኮት
ከመድኃኒአለም /2/
ጋሻውን ይዞ በፈረስ /2/
ከዘንዶ አስጣላት ብሩክታይትን ቅዱስ
ጊዮርጊስ /2/

66. ተወልደ

ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀህ በማይ /2/
ወለደነ ዳግመ እማይ /2/ ዳግመ /2/
ወለደነ ዳግመ እማይ
ትርጉም፦ ክርስቶስ ተወለደ፣ ክርስቶስ
ተጠመቀ
ዳግም ከውሀ ወለደን

67. ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ

ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ
መሰላል ነሽ የወርቅ መሰላል ነሽ
ሰውና አምላክን ያገናኘሽ
አዝ……..
አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ /2/
አሸተልቦት እንቅልፍ ተኝቶ ከጪዛ
ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ
መሰላል
ምሳሌሽን አየን ማርያም ድንግል
አዝ……..
መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ ከሰማይ /2/
እንዳየው ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ላይ
ተስፋ አድርጎ ሲኖር የሰላሙን ዘመን
ይኸው ተፈፀመ ባንቺው በእናታችን
አዝ…….
በአንቺና በልጅሽ ሆነልን ሰላም /2/
በአንቺ ተፈፀመ የያዕቆብ ሕልም
ሰውና መላእክት ተለያይተው ሲኖሩ
በልጅሽ መወለድ በአንድ ላይ ዘመሩ

68.ከላይኛው ሀገር

ከላይኛው ሀገር ከሰማያት ወርዶ
ከድንግል ማርያም ዳግመኛ ተወልዶ
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው
ፍሬ /2/
ህዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ /2/
አዝ…….
ከግብፅ ሲመጣ ኖሮ ስደት
ናዝራዊ ለመባል ገባ ከናዝሬት
ሎሌው ወደ ጌታ ነው እንጂ የሚሄደው
/2/
ጌታ እንዴት ይሔዳል ወደ አገልጋዩ
ዘንድ /2/
አዝ……
አጠምቅ ነበር ባንተ ስም ሕዝብን
እንዴት ብዬ ላጥምቅ አንተን ጌታዬን
ከሳቴ ብርሃን ወልደ ለብሩክ /2/
ብለህ ለመናገር አጥምቀኝ እያልክ /2/
አዝ…….
እንደዚህ እያለ ሊያጠምቅህ በልብ
መንፈስ ቅዱስ መጣ በአምሳለ ርግብ
አብም መሰከረ በደመና ሳለ /2/
የምወደው ልጄ ይሄ ነው እያለ /2/